ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

የግንቦት 7 ድምጽ

www.ginbot7.org

ቀን ግንቦት 22 2000 ዓ.ም

የፈረደባቸው ነጻ ጋዜጠኞች፤ የፈረደበት ነጻ ፕሬስ

ዛሬ ጠዋት ረፋዳው ላይ የአዲስ ነገር ጋዜጠኞች፤ ኤዲተሩ- መስፍን ነጋሽ፣ ምክሉ- ግርማ ተስፋው፣ ዘጋቢ- ጽዮን በፖሊስ ቁጥጥር ስር መዋላቸውን የግንቦት ድምጽ ማወቅ ችሏል፡፡ የቀረበባቸው ክስ ባይታወቅም ፣‹ በተበከለ ምግብ ስለሞቱት ሰዎች› ጽዮን ባቀረበችው ዘገባ ነው የሚል ጥርጣሬ አለ፡፡

‹የሚገርመው ነገር ከእዚህ ጋዜጣ አዘጋጆች መሃል አንዱ ጌታቸው ረዳ የሚባለው ግለሰብ የመቀሌ ዩኒቨርስቲ አስተማሪ የነበረ፣ አሁን ግን ወደ አዲስ አበባ ተዛውሮ የበረከትና የሽመልስ ከማል የህግና የሚድያ አማካሪ ሆኖ ሳለ እንዲህ አይነቱ እርምጃ ያውም በወያኔ ኢ.ህአዴግ አይን ከቁም ነገር በማይቆጠር ጉዳይ ጋዜጠኞቹ ለመታሰር እንደበቁ መሆኑን. ዘጋቢያችን ጠቁሟል፡፡

‹አዲስ ነገር ከወያኔ ጥቃት እራሱን በመከላከል እንደ ጋዜጣ አድጋለሁ ብሎ የያዘው አቋም በገለልተኛ ነጻ ጋዜጣ ስም ለወያኔ/ኢህአዴግ የሚስማማ ሆኖ እራሱን ማቅረብ እንደሆነ የጠቀመው ዘጋቢያችን፣ እንዲህ አይነቱ አካሄድ ከወያኔ/ኢህአዴግ ማንነት ጋር የማያወጣ እንደሆነ ጋዜጣው አልገባውም› ብሏል፡፡

በማከታተልም ‹ዛሬ በአዲስ ነገር ጋዜጠኖች ላይ የተፈጸመው አፈና፣ ነጻው ፕሬስ ነጻነትንና ዴሞክራሲን በሚመለከት ገለልተኛ መሆን እንደማይችል፣ በሃገሪቱ የዴሞክራሲና የነጻነት ጠር የሆነውን የመለስን አገዛዝ ከተቃወሚዎች ጋር እኩል በማስቀመጥ ሁለቱን ጥፋተኛ እያደረገ፣ ህዝብ በሁለቱም ላይ ጥርጣሬ እንዲኖረው በሚያደርግ መንገድ ጋዜጣው ማሰራጨት የጀመረው አመለካከት ወያኔን ከማገልገል አልፎ ጋዜጣውን የሚጠቅም እንዳልሆነ ዛሬ በገዛ ጋዜጠኖቹ ላይ ከደረሰው አፈና በፍጥነት ሊማር ይገባዋል› በማለት ዘጋቢያችን ደምድሟል፡፡